# ትንሣኤ ሙታን

ከብርሃኑ ጉበና

ሰው ሙቶ ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድና ከሃሊነት አካል ሠርቶ ነፍስ ዘርቶ ሕያው ሆኖ ይነሣል። ሥጋና ነፍስ በመጨረሻው ዘመን እንደገና ተዋሕደው ዳግመኛ በማይፈርስና በማይበሰብስ ሥጋ የሚነሡ መሆናቸውን የሚገልጸው የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ትንሣኤ ሙታን ይባላል።

ስለ ትንሣኤ ሙታን ስናነሣ በቅድሚያ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር አለ። ይኸውም የሰውን ተፈጥሮ ነው። ሰው በስድስተኛ ቀን በዕለተ ዓርብ «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌ ያችን እንፍጠር» ዘፍ.1፥26። በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ከአራቱ ባሕርያት ሥጋና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠረ ነው።

ሥጋ ሟች ፈራሽ በስባሽ ሲሆን ነፍስ ግን እንደ መላእክት ፍጹም፤ የማትሞት፤ የማትፈርስ፤ የማትበሰብስ፤ ዘወትር ሕያው ሆና የምትኖር ናት። የነፍስን ሕያዊት መሆንም መጻሕፍት በየስፍራው ይመሰክራሉ።

«ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ» ማቴ. 10፥28። ከዚህ አባባል የምንረዳው አንድ ሰው ሞተ ሲባል የሚሞተው ሥጋ መሆኑን ነፍስ ግን የማትሞት መሆንዋን ነው።

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል...» የሐዋ.7፥59 በማለት ቅዱስ እስጢፋኖስ ነፍሱን ፈጣሪው እንዲቀበልና በክብር ሥፍራ እንዲያኖራት መጠየቁ የሥጋና የነፍስን ልዩነት ይገልጽልናል።

«በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው» 1ጴጥ.3፥19።

ጌታ በዕለተ ዐርብ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል ላሉት ነፍሳት ነጻነትን ማወጁን ቅዱስ ጴጥሮስ ገልጾልናል። ነፃነትን የሰበከው ለሞቱት ሰዎች ሥጋ ሳይሆን ነፍስ ነው።

«...እርስዋም ስትሞት ነፍስዋ በምትወጣበት ጊዜ...ዘፍ.35፥16። ስለ ራሔል ሞት በተገለጸበት በዚህ ስፍራ የሞትን ትክክለኛ ትርጉምና የነፍስን ሕያውነት መረዳት ይቻላል።

ሞት ማለት የሥጋና የነፍስ መለያየት ነው። የራሔል ነፍስ ከሥጋዋ መለየትዋ ተገልጿአል።

ታላቁ ነብይ ኤልያስም ትመግበው የነበረችውን መበለት ልጅ ከሞት ሲያስነሣው «አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ» ብሎ ነበር የጸለየው። ነገ.17፥19–23። በዚህም የብላቴናው ነፍስ በአጸደ ነፍስ እንደነበረችና ሞትም የሥጋና የነፍስ መለያየት መሆኑን ያስገነዝበናል።

የጌታ ወንድም የሚባለው ያዕቆብ ምግባርና ሃይማኖት የተዋሐዱ መሆናቸውን በምሳሌ ሲገልጽ «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ብሏል። ያዕ.2፥26። በዚህም ሞት ማለት የነፍስ ከሥጋ መለየት መሆኑን አረጋግጦልናል።

ከነፍስ የተለየው ሥጋ እስከ ጊዜ ምጽአት በመቃብር ፈርሶ በሰብሶ እንደሚቆር መጻሕፍት በየስፍራው ዘግበዋል።

«ደመና ተበትኖ እንዲሄድ እንዲሁ ወደ ሙታን ሥፍራ የሚወርድ አይወጣም ወደ ቤት ደግሞ አይመለስም ሥፍራውንም አያውቀውም እንዲሁም ሰው ከተኛ በኋላ አይቆምም ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ (ምጽአት እስኪሆን) በሥጋው ከእንቅልፉ አይነቃም አይሰማም» ኢዮብ.7፥9–10፤ ኢዮብ.14፥12–24።[1]

ከላይ በተገለጸው መሠረት ሰው በሥጋው በመቃብር ውስጥ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እንደ እንስሳት ፈርሶ በሰብሶ እንደሚቆይና በዕለተ ምጽአት ግን ሥጋው፤ አጥንቱ፣ ጅማቱ፣ የራስ ጥጉ ሁሉ በለበት ሥፍራ ተሰብስቦ ሕያዊት ነፍስ ተዋሕዳው እንደሚነሣ ነው።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ያመኑ ሁሉ የክብር ትንሣኤ እንደሚነሱ ሲያስተምር «እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ባልኩ ጊዜ ኹሉን ወደ እኔ እስባለሁ» ብሏል። ዮሐ.12፥32። በዚህ ተስፋ መሠረት የክብር ትንሣኤ ተነሥተን በዘለዓለም ሕይወትና ክብር ከሱ ጋር እንኖራለን።

## በኲረ ትንሣኤ

«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኵራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቷል። ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው» 1ቆሮ.15፥20–24።

ፍርድ ሰጪው ፍርድ ተቀባዩ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰውነቴን አሳልፌ ለሞት ልሰጣት በመቃብር ልጣላት ዳግመኛም ላስነሣት ሥልጣን አለኝና በፈቃዴ ሰውነቴን ለበጎች ቤዛ አድርጌ ስሕማም ለሞት እሰጣታለሁ ዳግመኛ አስነሣታለሁ» ዮሐ. 10፥14–18። ባለው ቃል መሠረት አስገዳጅ ሳይኖርበት በሰውነቱ የወደደውን ሊያደርግ ያሰበውን የተናገረውን ለመፈጸም ፊቱን ለጽፋት፣ ጀርባውን ለግርፋት፣ ራሱን በበትር ለመመታት፣ የሾኽ አክሊል ለመቀ

ዳጀት፤ አፉን ለመሪር ሐሞት፤ እጅና እግሩን ለችንካር፤ ጐኑን ለጦር በፈቃዱ ሰጥቶ ለካዱት ለሰቀሉት «ባለማወቅ ይሠራሉና አባት ሆይ ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው» ብሎ ከጸለየላቸው በኋላ «አባት ሆይ ነፍሴን በአንተ እጅ እሰጣለሁ» ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለየ። ዮሐ.19፥1-30።

በዚህ ጊዜ ምድር ተናወጠች፤ አዕባን ተፈተቱ፤ መቃብራት ተከፈቱ፤ ከቅዱሳን ወገን ብዙ ሙታን ተነሡ። የቤተ መቅደስ መጋረጃ ተቀደደ። ማቴ.27፥47-53።

ሦስት መዓልት ከሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ ሞትና መቃብርን፤ ኃጢአትና ሰይጣንን ከሥልጣናቸው ሽሮ፤ በክብር ተነሥቶ አዳምንና ልጆቹን ከእሥራታቸው ፈታቸው።[2]

## የትንሣኤ ሙታን ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትንሣኤ ሙታን መኖር በተለያየ ስፍራ ተጽፎ ይገኛል። ዐበይት ነቢያት ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው ነቢዩ ዳንኤል የሙታንን መነሣት አስመልክቶ ሲያስተምር «በምድር ትቢያ ውስጥ ከንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና» ዳን.12፥2።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስም «ሙታንም ሕያዋን ይሆናሉ። ሬሳዎችም ይነሣሉ። በምድር የምትኖሩ ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩ» ብሏል። ኢሳ.26፥19።

ጌታችንም በመዋዕለ ትምህርቱ የሙታን ትንሣኤ እንዳለ ሲያስተምር «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለክፉ ትንሣኤ ይወጣሉና» ብሏል ዮሐ.5፥28።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በላከው ክታቡ የሙታንን መነሣት አስመልክቶ ሲጽፍላቸው «ኢየሱስ እንደሞተና እንደ ተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና» ብሏል 1ተሰ.4፥14።

ይኸው የቤተ ክርስቲያን የንጋት ኮከብ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለ ትንሣኤ ሙታን አበክሮ ሲያስገነዝባቸው «ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና...እንዲያማ ካልሆነ ስለ ሙታን የሚጠመቁ ምን ያደርጋሉ? ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ ስለ እነርሱ የሚጠመቁ ስለምን ድር ነው? በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለኝ በእናንተ ትምክህት እየማልሁ ወንድሞች ሆይ ዕለት ዕለት እሞታለሁ። እንደ ሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር ከታገልሁ ሙታንስ የማይነሡ ከሆነ ምን ይጠቅመኛል። ነገር ግን ሰው ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም። የምትዘራውም ስንዴ ቢሆን ከሌላም ዓይነት የአንድ ቢሆን ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም። እግዚአብሔር ግን እንደወደደ አካልን ይሰጠዋል...» 1ቆሮ. 15፥20-58።

## የሙታን አነሣስ እንዴት ነው?

የሞትህ ተነሥ የሚል አዋጅ በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ይታወጃል። «ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላእክት አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና» 1ኛተሰ.4፥16።

የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው፤ ያለቀው የደቀቀው ሁሉ ራሱ በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል[3]

ሁለተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋሕደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ በድን ይሆናል። አጥንቶችና ጅማቶች ከሥጋና ከደም ጋራ ይያያዛሉ። እስኪነሡ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ይሆናሉ።

ሦስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቀዋሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጠጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጐድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈሉ ወንድ በአቅመ አዳም የሠላሳ ዓመት ጐልማሳ፤ ሴት በዐቅመ ሔዋን የአሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ ሆነው በጎም ይሁን ክፉ ሥራቸውን ይዘው ይነሣሉ። ጌታ ራሱ እንደተናገረው በጐቹን በቀኝ ፍየሎቹን በግራ ያቆማቸዋል። ማቴ.25፥31-46።

## በበግና በፍየል የተመሰሉት እነማን ናቸው?

ጻድቃን በበግ፤ ኃጥአንን በፍየል መስሎአቸዋል። እንዴት ተመሰሉ?

ሀ. በጐች በደጋ እንጂ በቆላ አይኖሩም። ደጋ ብርድ ውርጭ ያለበት ቢሆንም በጎች ይህን ይቋቋማሉ ጻድቃንም በመከራ ሥጋ እንጂ በተድላ ደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን ለወርቅ ለብር ብለው አይለውጡም። ፍየሎች በቆላ እንጂ በደጋ አይኖሩም ኃጥአንም በተድላ ደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን ለወርቅ ለብር ብለው ይለውጣሉ።

ለ. በጐች እረኛቸው ባሰማራቸው ሥፍራ እንደሚገኙ ጻድቃንም እረኛቸው ክርስቶስ ባሰማራቸው በአንዲት ሃይማኖት ጸንተው ይኖራሉ። ፍየሎች ግን እረኛቸው ባሰማራቸው ሥፍራ ጸንተው አይቆዩም። እንዲሁ

ሲባዙት እረኞቻቸውንም ያደክሙታል ኃጥእንም እንዲሁ በሃይማኖት በምግባር ጸንተው አይቆዩም።

## ሁሉም በየግብሩ ይነሣል

አንዳንድ ሰዎች የሙታን ትንሣኤ መኖሩን ያምኑና ጻድቃንና ኃጥአን በስህተት ተቀላቅለው አይነሡምን? የሚል ጥያቄ ሲጠይቁ ይሰማሉ። ሁሉም በየግብሩ ይነሣል እንጂ ጻድቁ ኃጥእ ኃጥኡ ጻድቅ ሆኖ አይነሣም። ጻድቃን በምድር ላይ ሳሉ በሠሩት የጽድቅ ሥራ እንደ ፀሐይ አብርተው እንደ ጨረቃ ደምቀው ይነሣሉ። ለዚህም በምሳሌነት የምን ጠቅሰው ኑግና ስንዴን ነው።

ኑግና ስንዴ በአንድነት ተቀላቅለው በአንድ መሬት ላይ ቢዘሩ ኑግ ኑግ ሆኖ ቢበቅል እንጂ ስንዴ ሆኖ አይበቅልም። ስንዴውም ስንዴ ሆኖ ቢበቅል እንጂ ኑግ ሆኖ አይበቅልም።

አውሬ የበላቸው ወንዝ የወሰ ዳቸውስ እንዴት ይሆናሉ? እነዚህም ቢሆኑ አይቀሩም። ይነሣሉ። ከትን ሣኤ የሚቀር ሰው የለም። አውሬ የበላው ሰው ሥጋው ከአውሬው ሥጋ ተለይቶ ይነሣል። ለዚሁ ማስረጃ የሚሆነን የአረርና እህል ተቀላቅሎ መዘራት ነው። አረርና እህል በአን ድነት ቢዘራ አረሩ እዚያው ሲቀር እህሉ ግን ይበቅላል። አውሬ የበላ ቸው የሰዎች ሥጋም በትንሣኤ ወቅት በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሰዎቹ ሥጋ ከአውሬው ሥጋ ተለይቶ ሲነሣ የአው ሬው ሥጋ ግን ትንሣኤ ስለሌለው ፈርሶ በስብሶ ይቀራል መክ.3፥21።

## ስለ ትንሣኤ ሙታን የሥነ ፍጥረት ምሳሌ

ለትንሣኤ ሙታን ምሳሌ የሚሆኑ ከሥነ ፍጥረታት በኩል ብዙዎች ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተገልጸዋል።

የሐኩራ የተባለ ትል አለ። ይህ ትል በሚሞትበት ጊዜ ራሱን ከጉድፍ ውስጥ አግብቶ ይቀብረዋል። ከራስ ከበሰበሰ በኋላ እንደገና ሕያው ሆኖ ይነሣል።

ፈልፈል የተባለው ፍጥረት በተወለደ በሰባተኛው ወሩ ይሞታል። እንደገናም ሕያው ሆኖ ይነሣል።

ፊንቁን የተባለ በዓረብ አገር የሚገኝ ዎፍ አለ። ይህ ዎፍ ብዙ የሚያስደንቅ ነገር አለው አምስት መቶ ዓመት ይኖራል። ከአምስት መቶ ዓመት በኋላ የሚሞትበት ጊዜ መድረሱን ያውቃልና በክረምት ወራት ብዙ አበባዎችን አከማችቶ ተሸክሞት ወደ ግብጽ ይመጣና (ኤሊዮስ) ከተባለው ቦታ ላይ ይቀመጣል። ከዚህ በኋላ ደረቱን በክንፉ እራግቦ ሲመታው ከሰውነቱ ውስጥ እሳት ይወጣል።

የበሰበሰውን አበባ ሲያቃጥለው ከእሳቱ ውስጥ ገብቶ አጥንቱ ሳይቀር መላ አካሉ ተቃጥሎ አመድ ይሆናል። ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ደመና ደምና ዝናም ይዘንምና የተቃጠለበት እሳት ይጠፋል። በዚህ ጊዜ ከአካላቱ የማይቃጠል አንድ ክፍል አለና ለአንድ ቀን ይሸታል። ወድያውም ከሥጋው ውስጥ ትል ይወጣል። ትሉም ክንፍ አውጥቶ አካል ይሠራና በሦስተኛው ቀን ፋፍቶና አድጎ በአቅራቢያው ላሉት ሰዎች ይታያቸዋል። ቀስ በቀስ አካላቱ ሲጠነክር ተመልሶ ወደ አገሩ ወደ ዓረብ ይመለሳል።[4]

[illegible]

ዋቢ መጽሐፍ

1. ዓምደ ሃይማኖት፣ ገጽ 163
2. የኢትዮጵያ [illegible] ገጽ 172
3. [illegible] ቁ. 91
4. መርሐ ጽድቅ ባሕለ ሃይማኖት፣ ገጽ 27።

## እርማት

ባለፈው የሐመር መጽሔት ዕትማችን (4ኛ ዓመት ቁ.1) ላይ በወጣው የእንደራቻ መድኃኔዓለም ገዳም ታሪክ ላይ የተፈጠሩ አንዳንድ ስህተቶችን እናርም ዘንድ በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የካፈቶ ዞን ባህልና ስፖርት መምሪያ እና መ/ር ተመስገን በቀለ (ከቦንጋ) የላኳቸው ደብዳቤዎች ደርሰውናል። ስሕተቶቹ የተፈጠሩት በታይፐ ስሕተት ምክንያት መሆኑን እየገለጽን ለተፈጠሩትም ስሕተቶች ይቅርታ እንጠይቃለን።

### ማስተካከያ

| ገጽ | አንቀጽ | መስመር | ግድፈት | ማስተካከያ |
|---|---|---|---|---|
| 14 | 1 | 3 | የከቾና | የካፈቾና |
| 14 | 2 | 3 | ዲንቻና ጎቻ | ባርታና ጎቻ |
| 14 | 2 | 11 | የበርታ | የባርታ |
| 14 | 3 | 6 | 1932 | 1532 |
| 14 | 3 | 6 | ገዳመ | ገደማ |
| 14 | 3 | 8 | የጊዲ | የጊዲ |
| 14 | 8 | 10 | በተርአቹ | በተርበቾ |